Maryland's Largest School District

# MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS

*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

**ስለ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የ "ፀረ-ዘረኝነት ስርዓት አቀፍ ኦዲት" በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች**

ጃኑዋሪ 28፣ 2022 የተሻሻለ ሲሆን፥ (ተጨማሪ ጥያቄዎች ሲደርሱን ይህ ሰነድ እንደገና ማሻሻያ ሊደረግለት ይችላል)

**የፀረ-ዘረኝነት ስርዓት አቀፍ ኦዲት ምንድን ነው?**

- የዘር እና ዘረኝነትን ተፅእኖ ለመረዳት የዲስትሪክታችንን ፖሊሲዎች እና ልምዶች ግምገማ ማድረግ ነው።
- ይህ ግምገማ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) ስድስት የአሠራር ዘርፎችን ይመለከታል።

**ኦዲት የሚያደርገው ማነው?**

- ኦዲቱ የሚካሄደው በ Mid-Atlantic Equity Consortium (MAEC)፣ Inc. ከ MCPS Office of Strategic Initiatives ጽ/ቤት ጋር በመተባበር ነው።
- MAEC ኦዲት እንዲያካሄድ የተመረጠው ተማሪዎችን፣ ወላጆችን፣ ሰራተኞችን፣ አስተዳዳሪዎችን እና የማህበረሰብ ድርጅቶችን ባካተተ የባለድርሻ አካላት ኮሚቴ ነው።

**MCPS በስርዓት አቀፍ ፀረ-ዘረኝነት ኦዲት ውስጥ የሚሳተፈው ለምንድነው?**

- የዘር ልዩነቶች በሁሉም የ MCPS የአሠራር ዘርፎች ከንባብ አንስቶ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የትምህርት ክፍሎች ለመሳተፍ፣ የሚመረቁ ተማሪዎች ብዛት፣ የእገዳ እና የዲሲፕሊን ቅጣት መጠን እና የሰው ሃይል ምደባና አቅርቦትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ልዩነቶች ሊታዩ ይችላሉ። እንዲሁም በትምህርት ቤቶቻችን በርካታ የዘረኝነት ክስተቶች አጋጥመውናል።

**በወረርሽኝ መካከል ይህንን ኦዲት ማካሄድ ለምን አስፈለገ?**

- የባለድርሻ አካላት የዳሰሳ ጥናቶቹ መጀመሪያ ታቅዶ የነበረው ፎል 2021 እንዲጠናቀቁ ነበር፥ ነገር ግን በኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክንያት ትምህርት ቤቶች እና ቤተሰቦች ባጋጠሟቸው ተጨማሪ ስራ እና የተለያዩ ጫናዎች ምክንያት ብዙ ጊዜ ዘግይቷል/ቆይቷል።
- ወረርሽኙ ሁሉንም ሰው ቢያጠቃም፣ አገር አቀፍ እና የ MCPS መረጃ እንደሚያሳየው ኮቪድ-19 ከለር ቤተሰቦች ላይ ያልተመጣጠነ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳደረ መሆኑን ያረጋግጣል። ወረርሽኙ በአካዳሚያዊ እና ማህበራዊ-ስሜታዊ ተፅእኖዎች የሚያስከትለውን ጉዳት ለመፍታት ከፈለግን ስለ ዘር ተፅእኖ የበለጠ መረዳት አለብን። ስለዚህ ኦዲቱን ከዚህ የበለጠ ማዘግየት አንችልም።

**መረጃው የሚሰበሰበው እንዴት ነው?**

- አዲቱ በአራት የመረጃ መሰብሰቢያ ደረጃዎች የተከፋፈለ ነው።
    - ሁሉንም በሥራ ላይ ያሉትን ወቅታዊ ሰነዶች፣ ፖሊሲዎች እና ሪፖርቶች መገምገም።
    - በሁሉም የት/ቤት እና የዋና ጽ/ቤት አመራር ቡድኖች የተደረገ የዳሰሳ ጥናት።
    - ከ 4ኛ እስከ 12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና ሰራተኞች በሙሉ የዳሰሳ ጥናት ማድረግ።
    - ልዩ ትኩረት ከሚያሻቸው ቡድኖች እና ታወንሆልስ የማህበረሰብ ስብሰባዎች።

**በተገኙት ውጤቶች MCPS ምን ያደርጋል?**

- የኦዲት አማካሪው "Mid-Atlantic Equity Consortium, Inc. (MAEC)"፣ የመጨረሻ ሪፖርታቸውን ሰኔ 2022 ያቀርባሉ።
- የኦዲት ሪፖርቱን ቅድመ ዝግጅት በሚመለከት የኦዲት ግኝቶችን ለመረዳት፣ ህብረተሰቡን ለማወያየት እና ለውጦችን ለመተግበር የሚያስፈልጉ አወቃቀሮችንና ስልጠናዎችን ለማዘጋጀት ኮሚቴ እየሰራ ነው።
- በእያንዳንዱ ዘርፍ የተገኘ የኦዲት ውጤት ላይ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች ለመምከር እና ዲስትሪክቱ መውሰድ ስላለበት እርምጃ ከሰራተኞች፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች የተውጣጣ ቡድን ጋር ምክክር ይደረጋል። ኮሚቴዎቹ፣ ለምሳሌ የገንዘብ ድጋፍ እና የሰው ሃይል ለውጦችን፣ የፖሊሲ ማሻሻያዎችን፣ አዲስ ስልጠናዎችን እና የሰራተኞችን የስራ አፈጻጸም ደረጃዎች ለውጦችን ግምት ውስጥ ማስገባት ይችላሉ።
- በዚህ ሠመር ሁሉም የ MCPS ትምህርት ቤቶች እና ቢሮዎች የድርጊት መርሃ ግብሮችን ያዘጋጃሉ።
- ይህ ድረ ገጽ የተወሰኑ የድርጊት መርሃ ግብሮች እና የድርጊት ማሻሻያዎች ይቀርብበታል።

**ተማሪዎች የዳሰሳ ጥናቱን እንዴት መውሰድ ይችላሉ?**

- ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቤት ክፍል ውስጥ የዳሰሳ ጥናት ይወስዳሉ። እያንዳንዱ ትምህርት ቤት ከማርች 1 እስከ ማርች 31፣ 2022 ባለው ጊዜ ውስጥ የዳሰሳ ጥናቱን በየትኛው ክፍለ ጊዜ እንደሚሰጥ ይወስናል።
- የዳሰሳ ጥናቶች የራሳቸውን Chromebook በመጠቀም በኦንላይን ይወስዳሉ።
- የዳሰሳ ጥናቱን ከመውሰዳቸው በፊት ሁሉም ተማሪዎች ይህን ቪዲዮ ይመለከታሉ።

**ልጄ የዳሰሳ ጥናቱን እንዲወስድ/እንድትወስድ የማልፈልግ ከሆነስ?**

- ሁሉም ወላጆች እና አሳዳጊዎች ተማሪያቸው ጥናቱን እንዲወስድ ካልፈለጉ የተማሪ መርጦ የመውጣት ቅጽ የመሙላት አማራጭ አላቸው።
- ይህ ቅጽ ፌብሩዋሪ 18፣ 2022 መጠናቀቅ አለበት።
- የዳሰሳ ጥናቱን የማይወስድ ማንኛውም ተማሪ በ Chromebook ላይ ከእድሜ ጋር የሚመጥን ሌላ ተለዋጭ ሥራ ይቀርብለ(ላ)ታል።

**የዳሰሳ ጥናቶች ከእንግሊዝኛ ውጪ በሌሎች ቋንቋዎችም ይሰጣሉ?**

- አዎ፥ ሁሉም ባለድርሻ አካላት የዳሰሳ ጥናቶችን በአማርኛ፣ ቻይንኛ፣ ፈረንሳይኛ፣ ኮሪያኛ፣ ማንዳሪን፣ ስፓኒሽኛ፣ ቬትናምኛ፣ እና በፖርቹጋልኛ ማግኘት ይችላሉ።

**የዳሰሳ ጥናቶቹ ሲከናወኑ በስም-የማይገለጹ ናቸው?**

- አዎ፥ የዳሰሳ ጥናቶቹን የሚሞሉት ስማቸው ይፋ አይደረግም። የተማሪዎች ወይም የሰራተኞች ስም ወይም መለያ ቁጥሮች አይሰበሰቡም። ተሳታፊዎች የትምህርት ቤታቸውን እና የስነ ሕዝብ ስብጥር መረጃ እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ።

**የዳሰሳ ጥናቱ ምን ያህል ጊዜ ይወስዳል?**

- በግምት 15 ደቂቃዎች።

**የዳሰሳ ጥናት ጥያቄዎች እንዴት ነው የተዘጋጁት? ማን ነው አስተዋጽኦ ያደረገው?**

- የጥያቄዎቹ የመጀመሪያ ረቂቅ የተዘጋጀው የ MCPS ፖሊሲዎች ሰፊ ግምገማ ከተጠናቀቀ በኋላ በ MAEC ነው። MAEC በኦገስት እና ዲሰምበር 2021 መካከል የተሰበሰበውን ግብረመልስ ከተቀበለ በኋላ የዳሰሳ ጥናቱ እንዲከለስ ተደርጓል፦
  - MAEC ኦገስት እና ሴፕቴምበር 2021 ላይ ከተማሪዎች እና ከአስተማሪዎች የትኩረት ቡድኖች ጋር ውይይት አካሂዷል።
  - MCPS Equity Initiatives Unit ሁሉንም የዳሰሳ ጥናቶች በመገምገም ግብአቶችን ሰጥቷል።
  - ተማሪዎችን፣ ወላጆችን፣ ሰራተኞችን፣ አስተዳዳሪዎችን እና የማህበረሰብ ድርጅቶችን ያቀፈው የፀረ-ዘረኝነት ስርዓት አቀፍ ኦዲት አስተባባሪ ኮሚቴ ሁሉንም የዳሰሳ ጥናቶች ከገመገመ በኋላ ሰፊ ግብረመልስ ሰጥቷል።
  - ከሚከተሉት ቡድኖች ተወካዮች ተጨማሪ ግብረ መልሶች ተሰጥተዋል።
    - የቻይና አሜሪካውያን ወላጆች ማኅበር፣ የአይሁድ ማኅበረሰብ ግንኙነት ምክር ቤት፣ የላቲኖ ተማሪዎች ስኬት የድርጊት ቡድን፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የወላጅ መምህራን ማኅበራት ምክር ቤት፣ እና የከለር ህብረተሰብ የወላጆች ምክር ቤት ብሄራዊ ማህበር። "The Chinese American Parents Association, the Jewish Community Relations Council, the Latino Student Achievement Action Group, Montgomery County Council of Parent Teacher Associations, and the National Association for the Advancement of Colored People Parents Council"
- ከ MCPS Office of Shared Accountability የማጠቃለያ ግብአት ተሰጥቶበታል።

**ያሉትን ልዩነቶች ችግር ለመፍታት የኦዲት ውጤቱን መጠበቅ ይኖርብናል?**
**MCPS አሁን እርምጃ የማይወስደው ለምንድነው?**

የኦዲት ውጤቶቹ ከታወቁ በኋላ ሁሉን አቀፍ እቅድ ስለሚቀረጽ፣ MCPS የልዩነት ክፍተቶችን ለመፍታት ብዙ ጥረት እያደረገ ነው። የሚከተሉት ተግባራዊ የተደረጉ ድርጊቶች ናሙና ናቸው።

  - የፍትሃዊነት ማረጋገጫ ጥያቄዎች ቀርበው በዋና ጽ/ቤት እና በት/ቤት እቅዶች አፈጻፀም ላይ እየተለመደ መጥቷል። የነዚህ ጥያቄዎች አላማ የተማሪዎች እና የቤተሰቦች ፍላጎቶች በሁሉም የውሳኔ አሰጣጥ ደረጃዎች ላይ ተግባራዊ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው።
  - ሰራተኞች ስለ ፍትሃዊነት ስልጠና እንዲወስዱ ይጠበቅባቸዋል። የሚያስፈልጉት የሥልጠና ኮርሶች የሚከተሉት ናቸው፦

        - "Bridge from Implicit Bias to Antiracism – Summer 2021" ከስውር አድልኦ ወደ ፀረ ዘረኝነት ድልድይ - 2021 ሠመር በሁሉም የ 10 ወር ሰራተኞች መወሰድ ያለበት ኮርስ ነው
        - በሠራተኞች አቀጣጠር ላይ የሚደረግ አድሎአዊ አመለካከት - የበጀት ዓመት 2020 - በትምህርት ቤት ኦንላይን የቃለ መጠይቅ ፓነል ላይ የሚሳተፍ ማንኛውም ሰው ተሞክሮ፣
        - ስውር አድልኦን ማቋረጥ – የበጀት ዓመት 2019 – በሁሉም ሰራተኞች ኦንላይን መወሰድ ያለበት ኮርስ
        - ስውር አድሎአዊነትን መፈተሽ/መመርመር - የበጀት ዓመት 2018 - በሁሉም ሰራተኞች በአካልም ሆነ በኦንላይን መወሰድ ያለበት ኮርስ።
    - "The Equity Initiatives Unit" ለጽ/ቤቶች እና ለትምህርት ቤቶች ሞጁሎች፣ የጥናት ክበቦች፣ የፍትሃዊነት ጉዳዮች ጋዜጣ እና የእኩልነት ጉዳዮች ውይይትን በሚመለከት ቀጣይነት ያለው ድጋፍ ይሰጣል።

**ይህ በዘረኝነት ላይ ብቻ እንጂ ሌሎች አድሎአዊ እና የጥላቻ ድርጊቶች ላይ ያላተኮረው ለምንድነው?**

- ሁሉም የጭቆና ዓይነቶች ጎጂ እንደሆኑ እና በተማሪዎቻችን እና በሰራተኞቻችን አካዴሚያዊ እና ማህበራዊ ስሜታዊ ገጽታዎች ላይ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ በጥብቅ እናምናለን። ሆኖም፣ አንድ ሂደት ሁሉንም ዓይነት ጭቆናዎች በብቃት ሊፈታ ይችላል ብለን አናምንም። መረጃውን በሚመለከቱበት ጊዜ የዘር ልዩነቶች በሁሉም ዘርፎች (በጎሳ፣ በፆታ፣ በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚይዊ አቅም፣ በቋንቋ ብቃት ወይም በአካል ጉዳተኝነት) ላይ የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ሊታዩ ይችላሉ። ስለዚህ፣ በዘረኝነት ስርአት አቀፍ ተፅእኖ ላይ በማተኮር፣ በሁሉም የተገለሉ ቡድኖች ውጤቶች ላይ ተጽእኖ የሚያሳድሩትን የስርአት አቀፍ ኢፍትሃዊነትን ለመመርመር ሌንሶች እና መሳሪያዎች ይኖሩናል።

**MCPS ስለ ዘር እና ዘረኝነት ምን ያስተምራል?**

- MCPS የሁሉንም ማህበረሰቦች እና ባህሎች ልምድ በትክክል በሚያንፀባርቅ መነጽር የሀገራችንን፣ የተቋማቱን እና የፖሊሲዎችን ዝግመታዊ ለውጥ ለመመርመር ለተማሪዎች ከእድሜአቸው ጋር የሚመጥኑ መሳሪያዎችን ለመስጠት ዝግጁና ቁርጠኛ ነው።
- ሁሉም ተማሪዎች ያለፈውን ታሪክ እንዲያስቡ፣ አሁን ያላቸውን እንዲፈትሹ እና እርስ በርስ አጋር እንዲሆኑ እና ከዘረኝነት ልማዶች፣ አመለካከቶች እና ስርዓቶች የጸዳ የወደፊት ህይወት እንዲሰፍን እናበረታታለን።

**MCPS ስለ "Critical Race Theory" ስለ ዘር ነቀፌታ እሳቤ/ቲዎሪ ያስተምራል?**

- MCPS የ "Critical Race Theory"/ስለ ዘር ነቀፌታ እሳቤ/ቲዎሪ ሥርዓተ ትምህርት አያስተምርም ወይም አያስተዋውቅም።

**MCPS ዘረኝነትን እና ፀረ ዘረኝነትን እንዴት ይገልፃል?**

- ዘረኝነት የአንድን ዘር ቡድን ለመጥቀም በሌላኛው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ጥቅም ላይ የሚደረግ ስርዓት አቀፍ ጭቆና ነው። ዘረኝነት በተለያዩ ደረጃዎች ይገለጻል:- ውስጣዊ፣ ግለሰባዊ፣ ተቋማዊ እና መዋቅራዊ።

- ፀረ ዘረኝነት የቀለም ማህበረሰቦችን ተመጣጣኝ ባልሆነ መንገድ የሚጎዱ የዘረኝነት ድርጊቶችን፣ ፖሊሲዎችን እና አመለካከቶችን በመለየት፣ በማክሰም እና በማፍረስ የዘር ፍትህን ለማረጋገጥ እየሰራ ነው።
- ፀረ ዘረኝነት ማለት፡-
    - እምነታችን፣ ልምዶቻችን እና ግንኙነቶቻችን በዘር ፍትሃዊ ላልሆኑ ውጤቶች እንዴት አስተዋፅዖ እንደሚያበረክቱ በመግለጽ በየእለቱ ቁርጠኝነትን ማሳየት።
    - በምንሰራበት እና በምንኖርበት ማህበረሰቦች መካከል ዘረኝነት በትውልዶች ላይ ያደረሰውን ጉዳቶች እና በደሎችን እውቅና መስጠት።
    - የአንዱን ባህል የበላይነት ማንፀባረቅና ቅድሚያ መስጠት የዘር እኩልነትን ለመገደብ እና ለዘረኝነት እንዴት አስተዋጽኦ እንደሚያደርግ መረዳት።
    - በአውድ ውስጥ ያሉ የዘር ኢ-ፍትሃዊነትን መለየት እና ከሰራተኞች፣ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ አባላት ጋር በመተባበር ችግሮቹን መፍታት እና እርስ በእርስ ተጠያቂነትን ማስፈን።
    - ለተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና የቀለም ቤተሰቦች ተደራሽነትን፣ እድሎችን እና ፍትሃዊ ስኬቶችን የሚከለክሉ የዘረኝነት ፖሊሲዎችን፣ ልምዶችን እና አሠራሮችን ማምከን እና ማስወገድ።
    - ለተማሪዎች፣ ሰራተኞች እና የቀለም ቤተሰቦች ተደራሽነት፣ እድሎችን እና ፍትሃዊ የትምህርት፣ ማህበራዊ-ስሜታዊ እና የጤና ስኬቶችን የሚፈጥሩ አዳዲስ አሰራሮችን እና ፖሊሲዎችን በንቃት ማዳበር።

**ፀረ ዘረኝነት በነጮች ተማሪዎች ላይ ጉዳት ያደርሳል?**

- ፀረ-ዘረኝነት ማለት የፀረ-ነጭ ኮድ አይደለም። MCPS የሁሉንም ማህበረሰቦች እና ባህሎች ልምድ በትክክል በሚያንፀባርቅ መነጽር የሀገራችንን፣ የተቋማቱን እና የፖሊሲዎችን ዝግመታዊ ለውጥ ለመመርመር ለተማሪዎች ከእድሜአቸው ጋር የሚመጥኑ ትምህርታዊ መገልገያዎችን ለመስጠት ቁርጠኛ ነው።
- ነጮችን ብቻ ጀግኖች ወይም ክፋት ያለበት ሰው አድርገው የሚገልጹ ሥርዓተ ትምህርቶች እና የመማሪያ መጻሕፍት፥ የቀለም ሰዎችን ታሪክ እና አስተዋጽዖአቸውን የዘነጉ እና የተሳሳቱ ናቸው።